ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church of Our Savior
4401 Minnehaha Avenue South ♦ Minneapolis, MN 55406
Tel (612) 721-1222

«እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉስ ነው፥ በምድር መካከል መድኃኒትን አደረገ። አንተ ባሕርን በኃይልህ አጸናሃት፤»
መዝ ፸፫፥ ፸፬) ፥ ፲፪-፲፫ Ps. 74: 12-13

04/20/2015 እ.ኤ.አ
ቁ. ደ/ሰ/መ/ዓ/0031/15

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን
## ክርስቶስ በኃይሉና በሥልጣኑ ሞትን ድል አድርጎ ተነስቷል።

## <u>ወቅታዊ መግለጫ</u>

የሚኒሶታ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሊቢያ በሚገኙ የእምነታችን ተከታዮች ላይ ራሱን አይ ኤስ እያለ በሚጠራው አሸባሪ ቡድን የተፈጸመባቸውን ዘግናኝ እና አሳዛኝ ግድያ በጽኑ ታወግዛለች።

በቀደሙት ዘመናት አባቶቻችን ቅዱሳን ሰማእታት ስለ እምነታቸው ሲሉ፣ ስለ ክረስቶስ ፍቅር ሲሉ፣ ስለ ቤተክርስቲያን ሲሉ በአላውያን ነገሥታት እና አሕዛብ መከራን ተቀብለዋል፣በመጋዝ ተሰንጥቀዋል፣ በእሳት ተቃጥለዋል፣ በፈላ ውኃ ተቀቅለዋል። ደማቸውንም ስለመንግሥተ ሰማያት ሲሉ አፍስሰዋል።

በክርስትና ጉዞ ውስጥ እንዲህ አይነቱ ሰማእትነትና ለእምነት መሞት አዲስ አይደለም። ጌታችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስሙ አምነው የሚኖሩ ሁሉ በአለምና በአሕዛብ ዘንድ እንደሚሳደዱና እንደሚገደሉ አስቀድሞ አስተምሮናል።

"በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል፥ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ። በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ እርስ በርሳቸውም አሳልፈው ይሰጣጣሉ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ፤ ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች። እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።" ማቴ. 24፡ 9-13 በማለት በቅዱስ ወንጌሉ አስተምሮናል። ይህንን የጌታችንን ቃል በልባቸው ጽላት ላይ የጻፉ ወንድሞቻችን የእምነት ጽናት ምን ማለት እንደሆነ እንዳባቶቻችን ሰማእታት ዛሬ በሊቢያ በረሃ ውስጥ በተግባር አሳይተውናል። እውነተኛ የክርስቶስ ምስክርነታቸውንም በደማቸው ጽፈው ከቅዱሳን ሕብረት ተቀላቅለዋል።

የኢትጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንም ልጆቿን እንዲህ በእምንነት እና በጽናት የምታሳድግ መሆኗንም ለዓለም መስክረዋል። በዚህ አረመኔያዊ የአሕዛብ ድርጊት እኛ ክርስቲያኖች በፍጹም የምንሸበርና እምነታችንን የምንክድ አይደለንም።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ እነዲህ እያለ በእግዚአብሔር ቃል መክሮናልና፦ "በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ፤ ይህም ለእነርሱ የጥፋት፥ ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው፥ ይህም ከእግዚአብሔር ነው፤ ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤" ፊል. ፤፡ 28-29

ይሁን እንጂ ዛሬ በተለያዩ ሃገራት ውስጥ በሚገኙ ኢትጵያውያን ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ግድያ እና መከራ ከምን ግዜውም የከፋ ሆኗል።

በአረብ ሃገራት በተለይም በሳውዲ አረቢያ፤ የእስልምና መሥራች በሆኑት በነብዩ መሐመድ ሃገር፤ ለነብዩ ቤተሰቦች የስደት ጥገኝነት በመስጠት ከሞት የታደገቻቸውን ሃገር ሕዝቦች እጅግ አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ በየጎዳናው በመግደል፣ በማሰቃየት፣ በማሰርና በማፈናቀል የሚፈጸመው ግፍ፣ እንዲሁም በቅርቡ በየመን በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ሞት እና መከራ፣ በተጨማሪም በደቡብ አፍሪካ በወገኖቻችን ላይ እየተካሔደ ያለው ከሰብአዊነት የወጣ አረመኔያዊ ተግባር ውስጣችንን እጅግ አቁስሎት ባለበት ሰዓት በሊቢያ በሚገኙ የእምነት ወንድሞቻችን እና ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ላይ በተፈጸመው ወደር የለሽ አረመኔያው የግድያ ወንጀል ደብራችን የተሰማትን ጥልቅ ሐዘን ትገለጻለች።

እነዚህ ወገኖቻችን በሃገራቸው ላይ ሰርተውና እንደልባቸው ተዘዋውረው ለመኖር ያሉት ሁኔታዎች የሚፈቅዱ ባለመሆናቸው የሚወዷትን ሃገራቸውን ጥለው በመሰደድ ለራሳቸውና ለወገኖቻቸው ቀን ለማውጣት እየተንከራተቱ የነበሩ እንደኛው ያሉ መጻተኞች ወንድሞቻችን ነበሩ። ይህም ለእኛ በሰው ሃገር በስደት ለምንኖር ኢትዮጵያውያን ምን ማለት እንደሆነ የምናውቀው በመሆኑ ሃዘናችንን እጥፍ ድርብ ያደርገዋል።

በአሁ ወቅት በሊቢያና እና በየመን እንዲሁም በደቡብ አፍሪካ ከሞት ተርፈው ያሉና በየእስር ቤቱ የሚንገላቱ ወገኖቻችንን ለመርዳት ቤተክርስቲያናችን በምትችለው አቅም ሁሉ ጥረት እንደመታደርግም ትገልጻለች።

እነኝህ ሰብአዊነት ፈጽሞ የሌላቸው አሸባሪዎች መርዛቸው በሃገራችን እንዳይዛመት፤ በሰላም እና በፍቅር የኖረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳይመርዙ መላው ሕዝበ ክርስቲያን እና ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተገቢውን ጥንቃቄና እርምጃ ሊወሰድ ይገባል በማለትም ታሳስባለች። እነኝህ ለገሃነም እሳት የተዘጋጁ እና የትኛውንም የእምነት ተቋም የማይወክሉ ደም ያሰከራቸው ሽብርተኞች ከኃሉ አምላካችን ፍርድ ፈጽሞ የሚያመልጡ አይደሉም። በመሆኑም በቀልን ሁሉ ለእርሱ ለአምላካችን እንተዋለን።

በመጨረሻም መላው የቤተክርስቲያናችን አባላት እና ካሕናት እንዲሁም የቤተክርስቲያና አስተዳደር ሰበካ ጉባዔ/ ቦርድ / በግፍ የተጨፈጨፉት ወንድሞቻችንን ነፍስ እግዚአብሔር በእረፍት ቦታ እንዲያኖርልን፤ ለቤተሰቦቻቸው እና ለመላው ሕዝበ ክርስቲያንም እግዚአብሔር የመጽናናት መንፈስ እንዲያድልልን ይጸልያሉ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባረክ፤ አሜን!

**4401 Minnehaha Avenue South ♦ Minneapolis, MN 55406 ♦ Tel (612) 721-1222**